የጤና ሚኒስቴር፣ ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH, ETHIOPIA

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
Ethiopian Public Health Institute

# የኮሮና ቫይረስ (የኮቪድ-19) በሽታ ምላሽ አሰጣጥን አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

ባለፉት 24 ሰዓት ውስጥ በተደረገው 943 የላብራቶሪ ምርመራ አንድ (1) ሰው በኮሮና ቫይረስ መያዙ ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ በሀገራችን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር መቶ ሀያ አራት (124) ደርሷል፡፡ የላብራቶሪ ምርመራው የተደረገው በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢኒስቲትዩት፣ በብሄራዊ የእንስሳት ጤና በሽታዎች ምርመራ ማዕከል፣ በአርማውር ሃንሰን የምርምር ተቋም፣ በኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ በአማራ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፣ በአዳማ ህብረተሰብ ጤና ምርምር እና ሪፈራል ላቦራቶሪ እና በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ላብራቶሪ የተከናወነ ነው፡፡ በሌላ መልኩ በትላንትናው ዘጠኝ (9) ሰዎች (8 ከአዲስ አበባ እና 1 ከባህርዳር) ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን በአጠቃላይ በሀገራችን ከበሽታው ያገገሙ ሰዎች ቁጥር ሃምሳ (50) ነው፡፡ የታማሚው ዝርዝር ሁኔታም እንደሚከተለው ቀርቧል፣

| ተ.ቁ | ዜግነት | መኖሪያ ቦታ | እድሜ | ፆታ | የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ | በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ግንኙነት |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 1 | እንግሊዛዊ (ትውልደ ኢትዮጵያ) | | 45 | ወንድ | ከእንግሊዝ የተመለሰና በአስገዳጅ ለይቶ ማቆያ ውስጥ ያለ | - |

## በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ የሁኔታ መግለጫ

| | |
| --- | --- |
| አጠቃላይ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 14,588 |
| በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 943 |
| በዛሬው ዕለት በበሽታ መያዛቸው በላብራቶሪ የተረጋገጠ | 1 |
| በአጠቃላይ በቫይረሱ ተይዘው በለይቶ ከህክምና ውስጥ ያሉ | 69 |
| በፅኑ ህክምና ላይ ያሉ | 0 |
| አዲስ ያገገሙ | 9 |
| በአጠቃላይ ያገገሙ | 50 |
| በበሽታው ሕይወታቸው ያለፈ | 3 |
| ወደ ሀገራቸው የተመለሱ | 2 |
| እስከ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር | 124 |

በዛሬው ዕለት ምርመራ ከተደረገላቸው 943 ሰዎች መካከል የኮሮና ቫይረስ የተገኘበት አንድ ግለሰብ ብቻ መሆኑ የበሽታው ሥርጭት መቀነሱንም ሆነ በሕብረተሰቡ ውስጥ የበሽታው ሥርጭት አለመኖሩን የሚገልጽ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እስካሁን ድረስ ምርመራ የተደረገላቸው እና ቫይረሱ እንዳለባቸው የተገለጸው በአብዛኛው በአስገዳጅ ለይቶ ማቆያ የነበሩ እና የተወሰኑት ደግሞ ቫይረሱ እንዳለባቸው ከታወቁ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ የነበራቸው ሰዎች ናቸው፡፡

የኮሮና ቫይረስ ሥርጭትን ለመከላከል ሕብረተሰቡ የሚከተሉትን ጥንቃቄዎች አዘውትሮ ከመተግበር መዘናጋት እንደሌለበት ጤና ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በጥብቅ ያሳስባሉ። ህብረተሰቡ የበሽታውን ስርጭት ግምት ውስጥ በማስገባት፡

- በቫይረሱ መያዛቸው ከተረጋገጡ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ግለሰቦች በአፋጣኝ በ8335 ወይም 952 በመደወል ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት እንዲያሳውቁ፣
- ለተለያዩ ጉዳዮች በአንድ ቦታ መሰባሰብ በማስወገድ፣ እጅን አዘውትሮ በመታጠብ፣ በአካል ንክኪ የሚደረግ ሰላምታን በመተውና አካላዊ መራራቅን ተግባራዊ በማድረግ የበሽታውን ስርጭት እንዲከላከል እናሳስባለን።

በማንኛውም ሰዓት ጥቆማ ለመስጠትና መረጃ ለማግኘት በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም በ952 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት በስልክ እንዲያሳውቁ እንጠይቃለን።

ዶ/ር ሊያ ታደሰ
የጤና ሚኒስትር

ሚያዝያ 19፣ 2012 ዓ.ም

የጤና ሚኒስቴር፣ ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH, ETHIOPIA